የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 36
ADDIS ABABA 15th May, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፱/፪ሺ፩ ዓ.ም

በባህር ላይ በሚጓጓዙ አደገኛና ጐጂ እቃዎች ሳቢያ ለሚደርስ ጉዳት ስለሚኖር ሃላፊነትና ካሳን አስመልክቶ የወጣውን አለም አቀፍ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ… ገጽ ፬ሺ፯፻፳፰

CONTENTS

Proclamation No. 629/2009

The Convention on the Liability and Compensation for Damage in Connection with the Carriage of Hazardous and Noxious Substances by Sea Ratification Proclamation Page 4728

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፱/፪ሺ፩

## በባህር ላይ በሚጓጓዙ አደገኛና ጐጂ እቃዎች ሳቢያ ለሚደርስ ጉዳት ስለሚኖር ሃላፊነትና ካሳን በሚመለከት የተደረገ አለም አቀፍ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ

በባህር ላይ በሚጓጓዙ አደገኛና ጐጂ እቃዎች ሳቢያ ለሚደርስ ጉዳት ስለሚኖር ሃላፊነትና ካሳን አስ መልክቶ የአለም አቀፉ የባህር ድርጅት ስምምነት እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፺፮ የወጣ ስለሆነ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክ ራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በባህር ላይ በሚጓጓዙ አደገኛና ጐጂ እቃዎች ሳቢያ ለሚደርስ ጉዳት ስለሚኖር ሃላፊ ነትና ካሳን አስመልክቶ የወጣው አለም አቀፍ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፱/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 629/2009.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE INTERNATIONL CONVENTION ON LIABILITY AND COMPENSATION FOR DAMAGE IN CONNECTION WITH THE CARRIAGE OF HAZARDOUS AND NOXIOUS SUBSTANCES BY SEA

**WHEREAS,** an International Convention on Liability and Compensation for Damage in Connection with the Carriage of Hazardous and Noxious Substances by Sea has been adopted by the International Maritime Organization in 1996;

**WHEREAS**, the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 30th day of April, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Convention on the Liability and Compensation for Damage in Connection with the Carriage of Hazardous and Noxious Substances by Sea Ratification Proclamation No. 629/2009".

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በባህር ላይ በሚጓጓዙ አደገኛና ጎጂ እቃዎች ሳቢያ ለሚደርስ ጉዳት ስለሚኖር ሃላፊነትና ካሳን አስመልክቶ የአለም አቀፍ ባህር ድርጅት እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፺፮ ያወጣው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሥልጣን

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Convention

The International Maritime Organization convention on liability and compensation for damage in connection with the carriage of hazardous and noxious substances by sea adopted in 1996, is hereby ratified.

## 3. Responsibility of the Ministry of Transport and Communications

The Ministry of Transport and Communications is hereby authorized to undertake in cooperation with the concerned governmental organs all acts necessary for the implementation of the convention.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of May, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**